መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

The Holy Trinity Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

## ከኖርዝ ካሎራይና መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ የአቋም መግለጫ።

“አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤” ዮሐ ፮:፴፯

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ፤ ይህም የሚታወቀው ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ ዘመናችን ትምህርቷ፣ ሕጓና ሥርዓቷ ሳይፋለስ በመኖሯ ነው። ይህም ኦርቶዶክሳዊት ወይም ርትዕት አሰኝቷታል። ቀጥ ያለ አስተምህሮ፣ ያልተዛባ ሕግና ሥርዓት፣ የቀና ሃማኖት ባለቤት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን በየዘመኑ በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት ይህንን መልኳን የሚያጠፋ ችግር አጋጥሟታል። ይሁን እንጅ ሁሉንም ሕዝቦቿ እግዝአብሔርን የሚወዱ በመሆናቸው ሲያቀኑት ኑረዋል። በእኛ ዘመንም ቤተ ክርስቲያን በሶስት ጎራ የተመደበችበት ዘመን ነው። ይህን ክፍፍል ወደ አንድነት ለማምጣት የመካነብርሃን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የራሷን ድርሻ ተወጥታለች፤ ለቤተ ክርስቲያንችን ሕግና ሥርዓትም መጠበቅ ቅድሚያ ትሰጥታለች። ስለዚህም ሥላሴን እናመሰግናለን።

በሻርለት ኖርዝ ካሎራይና የምትገኘው መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላለፉት 13 ዓመታት በገለልተኛነት መኖሯ ይታወሳል። በገለልተኛነት እንድትቆይ ያስገደዳትም ዋና ምክንያት ለአለፉት ሃያ ዓመታት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ማእከል በማድረግ የተፈጠረው ልዩነት ተወግዶ በተዋህዶ ይመለሳል በማለት ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች ዘንድ ታላቅ ተስፋ የተጣለበትና ለአለፉት ሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ ሲካሄድ የቆዬው የሰላም ድርድር ከፍጻሜ ድርሶ ለማየት ምኞታችን ፍጹም ነበር። ሆኖም ከዛሬ 21 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያን የተቆጣጠረው አካል በቤተክርስቲያናችን ላይ ያስገባውን ዕጅ መሰብሰብ ባለመቻሉና ለፍላጎቱም መጠቀሚያ የሚሆኑ ለግል ጥቅምና ስልጣን እንጂ ለቅድስት ቤተ ክስርቲያን አንድነት ድንታ የሌላቸውን አንዳንድ አባቶች ከጎኑ በማሰለፍ ብዙ የተደከመበትና ተስፋ የተጣለበት የሰላም ድርድር ያለውጤት እንዲቋጭ አድርጓል። ስለዚህ የመካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያናችን በገለልተኛነት መቆየት የታሰበውን አንድነት የሚያመጣ ሳይሆን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሳተ አካሄድ በማጠናከር ዕምነታችንንና የቤተ ክርስቲያን ስርዓታችን የሚያፋልስ በመሆኑ ለማስተካከል ተገዳለች።

ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንጻር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት የሚያሰኛት ከአባቶቻችን ሐዋርያት በተላለፈው ሥርዓትና ትውፊት መሠረት በተዋረድ መመራት ስትችል ነው። ይሁን እንጅ የመካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በገልተኛነት መኖር የቤተክርስቲያናችንን ኦርቶዶክሳዊነት የሚያዛባ ችግር የወለደው ጎጅ ልማድ መሆኑን ባለመገንዘብ በገልተኛነት እስከ ዛሬ የካቲት ፲፯/፳፻፭ ዓ/ም (Feb 24/2013) ቆይታ ነበር ። ነገር ግን «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» እንዳለ ቅዱስ ዳዊት «የእግዚአብሔር የራሱ የሥራ ጊዜ ስላለው» በዛሬው እለት በስደት ላይ የሚገኘው የሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስን የአንድነት ጥሪ ቤተ ክርስቲያናችን አክብራ በመቀበል ጠቅላላ የአባላት ጉባኤ ስብሰባ በማድረግ ውሳኔ አስተላልፋለች። በጠቅላላ የአባላት ጉባኤ ስብሰባ ላይ በገለልተኛነት መኖር በቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት እንዲሁም ሐዋርያዊ ትውፊት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ባለማወቃችን

9420 Idlewild Road, Charlotte, North Carolina 28227 Phone: 704-573-3431 kidistselassie@gmail.com

ለአለፉት 13 ዓመታት በገለልተኞነት ከሁለቱም የአስተዳድር መዋቅር ውጭ በመሆን ቆይተናል። ከዛሬ ጀምሮ ግን በብፁእ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በሚመራው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚተላለፈውን አመራር በመቀበልና በስደት ከሚገኙት አባቶቻችን ቡራኬ እየተቀበልን በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት መመራት እንዳለብን በሰፊው የአባላት ጉባኤው ስብሰባ ውይይት ተደርጎበታል። በዚህ ጠቃላላ የአባላት ጉባኤ ስብሰባ የመካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናኑ ካህናቱን ባስረጅነት በመያዝ ሰፊ ውይይት ካደረግን በኋላ በብፁእ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በሚመራው ከሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ለመሥራትና እንደ አባቶቻችንም ሥርዓት የቅዱስ ሲኖዶስን መንፈሳዊ መመሪያ እየተቀበልን ለመስራት ተስማምተናል። በዚህ መሰረት ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ የቤተ ክርስቲያናችን አቋም መሆኑን እንገልጻለን።

1. በአዲስ አበባ እየተከናወነ ያለው ሕገ ወጥ የስድስተኛ ፓትርያሪክ ሲመት የቤተ ክርስቲያን የሰላም በር የሚዘጋ በመሆኑና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የመከራና የልዩነት ዘመን የሚያራዝም በመሆኑ አጥብቀን እንቃወማለን የሚሾመውንም አባት የቤተ ክርስቲያን አባት ብለን የማንቀበላቸው መሆኑን ለሚመለከተው ሁሉ ለመግለፅ እንወዳለን።-ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አኳያ አባታችን በስደት ዓለም የሚገኙት ፬ኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ናቸው። የምንቀበለውም በቅዱስነታቸው የሚመራውን ሕጋዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

2. ከእውነተኛ አማኞች የሚጠበቀው ስለእውነት ተገቢውን ዋጋ በመክፈል ለእውንት መቆምና አንድነትን መጠበቅ እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ በራስ ሀሳብና ፍላጎት ላይ በመመሥረት ቤተ ክርስቲያንን ገለልተኛ ማድረግ አካለ ክርስቶስን መክፈል እንደሆነ በሌሎችም ዘንድ እስከ አሁን እንደኛ በገለልተኛነት አቋም በቆዩ ወገኖቻችን ሊታሰብበት ይገባል እንላለን። ምክንያቱም በብጹእ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ የሚመራውን ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስንና አመራሩን አለመቀበል የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ትውፊት የሚያጠፋ፤ ሥርዓት አልበኝነትን የሚያስፋፋና ኢቀኖናዊ በሆነ መንገድ ለሚጓዙ ሰዎች ዋና በር የከፈተ በመሆኑ መታረም ያለበት ጊዜ አሁን እንደሆነ እናምናለን። ስለዚህ እስከ አሁን ድረስ በገለልተኛንት አቋም የቆዩ አብያተ ክርስቲያናት ያለፈውን ስሕተት በማስተካከልና ትክክለኛውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥርዓትን በመከተል ከእግዚአብሔርና ከታሪክ ተጠያቂነት በመዳን ለልጆቻቸው ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት የሆነችውን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ማስረከብ ግዴታ እንዳለባቸው በዚህ አጋጣሚ ማሳሰብ እንወዳለን።

3. ምስጢረ ክህነት ከሰማያዊ አምላክ የተሰጠ ሰማያዊ ሐብትና ጸጋ በመሆኑ በክብር መያዝ እንዳለበት እናምናለን። በአባቶቻችን ሐዋርያት ሥርዓትና ትውፊት መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ ከሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ተለይቶ ገለልተኛ መባልና በገለልተኛነት መኖር በውስጧ የሚያገለግሉትን ካህናት_ሐዋርያዊ አገልግሎት ክህነትና እምነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል። ምክንያቱም በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት አንድ ሐዋርያ ካህን የቅዱስ ሲኖዶስን የሥራ መመሪያና ሕግ በማይቀበል ቤተ ክርስቲያን እንዳያገለግል በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተደንግጓል። ከቀኖና ቤተ

ክርስቲያን ውጭ በራሱ ፈቃድ አገልግሎት ቢሰጥ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲለይ እንደሚከተለው ፍትሐ ነገሥት ያዝዛል። «ካህን ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ ቢሄድ ሌላይቱ ቤተ ክርስቲያን አትቀበለው ። ወደቦታው ይመለስ ዘንድ ይማልዱት እንጅ፤ ሊመለስ ባይወድ ይለይ። በጉባኤም አይቀላቀል...አንዱ በራሱ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያኑን ቢተው ከእነርሱ ጋር ባለው ኤጲስ ቆጶስ ፈቃድ ካልሆነ በቀር፤ ስለዚህ ከክህነቱ ይሻር» ይላል /ፍትሐ ነገስት አነቀጽ ፯ ቁ ፻፺፪፤ ቁ ፻፺፫-፻፺፬፤ በመሆኑም እውነትን በመከተል ሕገ ቤተ ክስርስቲያንንም አክብሮ በመያዘ ለትውልድ ለማስተላለፍ ግዴታ እንጂ ወዴታ እንዳልሆነ እናምናለን።

4. በገለልተኛነት መኖር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀኖና ሥርዓት ውጭ የሚያደርግ መሆኑን በማመንና እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ክብር ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ከሐዋርያት ትምህርትና ሥርዓት ውጭ የሚያደርግና አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል መሆኑን በግልጽ ተረድተናል። የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት በመናድ አንድነታችንን በማዳከም ለማንኛውም ጥቃት አጋልጦ ይሰጠናል። ባጠቃላይ "ገለልተኝነት" ስርዓተ አልበኝነትን በማስፋፋት የቤተክርስቲያናችንን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን ስለተረዳን አንቀበለውም። ይህን ስርዓት የለቀቀ የገለልተኛነት አሰራር ለማስተካከል የሚደረገውን ጥረት ሙሉ በሙሉ እንደምንደግፍም ለመግለፅ እንወዳለን።

በዚህ ፈታኝ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር አንድ ሁነን ልናከብራትና ልናስከብራት ስለአንድነቷም ተግተን ልንሰራ ይገባል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነት መጠበቅ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የሰብዓዊ መብት ረገጣን ለማስወገድና በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር የተሰጠንን የስብዓዊነት ክብርና ጸጋ ለመላበስ ይረዳል ብለን እናምናለን። እግዚአብሔርም በአንድነት ለኢትዮጳያ ሀገራችን አንድነትና ክብር መመለስ የምናደርገውን ጥረት ሁሉ ይባርክልናል። ስለሆነም እኛ በሻርለት ኖርዝ ካሎራይና መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምንገኝ ካህናት መዘምራንና ምእመናን በሙሉ ከአባቶቻችን ጋር ሆነን በቀኖና ሐዋርያት የተደነገገውን እክብረን እናት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ለማገልገል እንድንችል ሥሉስ ቅዱስ ስለፈቀደልን እናመሰግነዋለን።
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ አሜን።

መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ሻርለት ኖርዝ ካሎራይና

የካቲት ፲፯ ቀን፳፻፫ ዓ.ም